



# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## የዕለቱ ምስባክ

ዐረገ እግዚአብሔር በይባቤ
ወእግዚእነ በቃለ ቀርን
ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ

አምላክ በእልልታ
እግዚአብሔር በመለከት ድምጽ ዐረገ
ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ

መዝ ፵፮፤፭-፮

ወንጌል፥ ሉቃስ ፳፬፤፵፭-ፍጻሜ
ቅዳሴ፥ የዲዮስቆሮስ ቅዳሴ (እምቅድመ ዓለም)

## የዕለቱ ትምህርት

# ዕርገት

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤ በኋላ አርባ ቀን ሐዋርያትን እያስተማረ ስለሚመጣው አጽናኝ እያስረዳ ሰነበተ (ዮሐ ፳፩፤፫)። ስለ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊውን ነገር እያስተካከለ አእማደ ቤተ ክርስቲያንን በማቆም የሐዲስ ኪዳን ሕግና ሥርዓትን ለማጽናት አርባ ቀን ቆየ፤ በቀደመው ኪዳን አምሳል (ዘፀ ፳፬፤፲፰ ። ፩ኛ ነገ ፲፱፤፰)። ክርስቶስ መለኮታዊ አሸናፊ በመሆን የድል አድራጊነት ምርኮውን ማርኮ ወደ ሰማይ አረገ። ምርኮዎቹም ዲያቢሎስን ድል ነስቶ የማረከን እኛ ነን (ኤፌ ፬፤፰)። «የሰጠከኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር ላይ አከበርኩህ» (ዮሐ ፲፯፤፬) ብሎት ነበር አባቱን ከመሞቱ በፊት።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዕርገቱ የመረጠው ቦታ ከዓለም ሳለ አዘውትሮ ይጐበኘው የነበረውን ቦታ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ከቤተ መቅደስ በመለየት የተመረጠችውን ከተማ እንደተወ ከኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ በሚገኘው የደብረ ዘይት ተራራ ላይ አረፈ። ክርስቶስም በተራራዋ ላይ ሆኖ ከተማዋን በርህራሄ ዓይን ተመለከተ። በዚህም ተራራ ላይ የነበሩ ደኖችና ሸለቆዎች በክርስቶስ ተቀድሰው ነበር። የዚህ ተራራ ሸንተረሮች ንጉሥ ክርስቶስ መሆኑን ያሰሙትን ድምጽ አስተጋብተዋል። በዚህ ተራራ ጥግ ላይ በምትገኝ በቢታንያ ከተማ ነዋሪ በሆኑት በእነ አልአዛር ቤት ብዙ ጊዜ አርፎ ነበር። በተራራው ግርጌ በምትገኘው የጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ ውስጥ ኢየሱስ በብዙ እንባና ጩኸት ጸልዮአል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ያረገው በዚህ ተራራ ላይ ሲሆን ዳግመኛም ሲመጣ እግሮቹ የሚያርፉት በዚሁ ተራራ ጫፍ ላይ ነው። ሁለተኛ ሲመጣ እንደተከዘ ሰው ሳይሆን እንደ ድል አድራጊ ንጉሥ ሆኖ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ሲያርፍ የዕብራውያን የሃሌሉያ መዝሙር ሆሳዕና ከሚለው መዝሙር ጋር ተቀናጅቶ ይዘመርለታል፤ ጻድቃንም በከፍተኛ ድምጽ ከነገደ መላእክት ጋር ይዘምሩለታል።

ከዕርገት እስከ ጰራቅሊጦስ፣ ከእርገት በኋላ ከጰራቅሊጦስ በፊት በሚውለው ሰንበት የሚፈጸመው ሥርዓተ አምልኮ የሚከተለውን ይመስላል።

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

በሰንበት ዐረገ ሐመረ
«በሰንበት ወደ መርከብ ወጣ»

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| ፩ | ሮሜ ፲፤፩-ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| ፪ | ፩ኛ ጴጥ ፫፤፲፭-ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| ፫ | የሐዋ ሥራ ፩፤፩-፲፪ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

ከጥቂት ሳምንት በፊት የአይሁድ አለቆች ለመስቀል ሞት አሳልፈው የሰጡት በክፉ አገዳደልም የገደሉት መሲህ ተማሪዎቹን እየመራ ወደ ቢታንያ ወሰዳቸው። ደቀ መዛሙርቱ ከጌታቸው ጋር የሚገናኙበት ቀን ይህ ብቻ መሆኑን አላወቁም ነበር። ለሚወዳቸውና ትቶአቸው ለሚሄድ ተከታዮቹ «እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» የሚል ተስፋ ሰጣቸው (ማቴ ፳፰፤፳)። ቢታንያ ሲደርስ መሄድን ትቶ ቆመ፤ ደቀ መዛሙርቱም ከበውት ቆመው ጌታም በፍቅር ዓይን አያቸው፤ እጆቹንም አንስቶ ሲባርካቸው ለማንኛውም ምድራዊ ስበት በበለጠ ኃይል ከመካከላቸው ተነስቶ ወደ ሰማይ አረገ። ደቀ መዛሙርቱም ጌታቸውን ዓይናቸው እስኪሰወርና ዓይኖቻቸው እስኪፈዙ ድረስ በአድናቆት እና በፍቅር ወደ ላይ ተመለከቱ። ወዲያውኑ የክብር ደመና ከዓይናቸው ሰወረው፤ የርቀት ያይደለ የርሕቀት መላእክትም የደመና ሠረገላዎች መስለው በተቀበሉት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ «እነሆ እኔ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ሲል የሰጣቸውን ተስፋ እያስታወሱ ጥኡም የሆነውን ዝማሬ መላእክት ሰሙ። መላእክትም «እናንተ የገሊላ ሰዎች ወደ ሰማይ ሲመጣ ያያችሁት ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል» የሚል ተስፋ አበሰሩአቸው። ክርስቶስ ሲያርግ ያዩት ተማሪዎች ልባቸው አብሮ አርጓል። ወደ ላይም መንፈሳቸው ተነጥቆአል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አገራቸው በሰማይ ሆኗል። ወደ ሰማይ ያረገው በእልልታ በዝማሬ መላእክት በመለከት ድምጽ ነበር። እንዲሁም ዓይን ሁሉ እያየው ይመጣል (ራዕ ፲፩፤፯ ። ፩ኛ ተሰ ፬፤፲፯ ። ማቴ ፳፭፤፴፩) በላይ በሰማይም ቦታ እንዳዘጋጀልን መጥቶ ይወስደናል (ዮሐ ፲፬፤፫)።

## የክርስቶስ እርገት ለእኛ ያለው ጥቅም

የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ «ዐረገ እግዚአብሔር ከመያለቡ ዕርገተ ጻድቃን … እግዚአብሔር ወልድ የጻድቃንን ዕርገት ያስገነዝብ ዘንድ አረገ» ያላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጌታችን ዕርገት የተጻፈውን እንመልከት፥ «ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ አረገ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ (ማር ፲፮፤፲፱)። እስከ ቢታንያም አወጣቸው እጆቹንም አንስቶ ባረካቸው ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ወደ ሰማይ ዐረገ (ሉቃ ፳፬፤፶-፶፩)። «ይህንንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው።

…. ወደ ሁለተኛው ገጽ ዞሯል።

እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ። ደግሞም የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሏቸው (ሐዋ ፩፥፱-፲፩)። ሠለስቱ ምእትም «ዐረገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ … በክብር በምስጋና ወደ ሰማይ አረገ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ» ብለዋል። በእርሱ ዕርገት ምድራውያን የነበርነው በሞት ከምድር ጋር የተቀላቀልነው ከፍ ከፍ አልን ሕይወታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ተሰወረ። «እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሳችሁ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም፤ ሞታችኋልና ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር በክርስቶስ ተሰውሯልና ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ (ቈላ ፫፥፩-፬) ተብሎ የተጻፈውን ቃለ መጽሐፍ ልብ እንበል። አሁን በሞቱ ሞትን (ለኃጢአት) በትንሣኤውም ተነሳን በዕርገቱም ዐረግን ሰማያውያን ሆንን። ሕይወታችንም ከኢየሱስ ጋር ወደ ሰማይ ተሰወረ (ዐረገ) በመምጣቱም ይለጣል። ከላይ የጠቀስነው የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ እንዳለው የኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት የጻድቃንን ዕርገት ያመለክታል። (ይህ ሁሉ ግን በተስፋ ነው።)

ቅደስት ቤተ ክርስቲያንም «ላእለ ይኩን ህሊናክሙ በሰማይ የሀሉ ልብክሙ አእምሩ ኀበ ዘትቀውሙ መስማኢ ቃለ ጽድቅ ወአስምኡ ዜና ሠናየ» በማለት ስትቀድስ ትሰማለች።

ትርጉሙም «ሕሊናችሁ በላይ ክርስቶስ ባለበት ይሁን ልባችሁም በሰማይ ይኑር የቆማችሁበትን እወቁ፤ የጽድቅ ቃልን ስሙ መልካም ዜና ወንጌልን አድምጡ» ማለት ነው።

## ስለ እኛ ባአባቱ ቀኝ ተቀመጠ

«ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተነጋገረ በኋላ ወደ ሰማይ አረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ» (ማር ፲፮፥፲፱)። «እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በስልጣኑ ቃል እየደገፈ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ (ዕብ ፩፥፫)። «ከተናገረውም ዋና ነገሩ ይህ ነው። በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን (ዕብ 8፥1) ተብሎ እንደ ተጻፈ ኢየሱስ ማረጉ ግልጥ ነው። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ከመለኮታዊ ክብሩ ተራቁቶ ኑሮ ወደ መለኮታዊ ክብሩ በተመለሰ ጊዜ የተራቆተ መለኮታዊ መንበሩን ተቆጣጠረ ለማለት ሳይሆን ይህ ቃል የሚያመለክተው እኛን ለማዳን ወደረ የተባለው ለምልአተ መለኮቱ ውሳኔ የሌለው እርሱ ሥራውን መጨረሱን በእርሱ ክብር መቀመጣችንን ነው የሚገልጸው። ተቀመጠ የተባለውም ክብር የለሽ የነበረውን የሰው ልጆችን ባሕርይ ነው የሚያመለክተው እንጂ ወልድ ለመለኮታዊ ዙፋኑማ አዲስ አይደለም፤ በአብ ቀኝ ኢየሱስ እንደተቀመጠ በመቀመጡም የከበርነውን ክብር በሚመለከት «በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስነሳን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን» (ኤፌ ፪፥፮-፯) ተብሎ የተጻፈውን ማንበብ በቂ መረጃ ነው።

በየማነ አብ የተቀመጠው ወልደ አብ ክርስቶስም ዕድል ፈንታችን ከእርሱ ጋር እንደሚሆን ተስፋ ሰጥቶናል፤ እንዲህ ብሎ፥ «የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል» (ዮሐ ፲፪፥፳፮)። «እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ» (ዮሐ ፲፬፥፫)። «ድል ለነሳው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ» ብሎ (ራዕ ፫፥፳፩) የሊቀ ካህንነት ጸሎቱንም ሲጸልይ «አባ እለሰ ወሀብከኒ እፈቅድ ከመየሀልው ኀበ ሀሎኩ አነ ምስሌዬ ከመ ይርአዩ ስብሐትዬ ዘወሃብከኒ» ብሏል። ይህም ማለት «አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድከኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ» (ዮሐ ፲፯፥፳፬) ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስም ይህንን ተስፋ በእምነት እንደምንወርስ ሲናገር «ወታበውእ ውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ኀበ ቦአ ኢየሱስ ሐዋርያነ በቅዳሜነ ሊቀ ካህናት … ከዊኖ ዘለዓለም» ብሏል (ዕብ ፮፥፳)። ይህንን ቃል ብሔራውያን፤ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት በአንድምታ ትርጉማቸው ሲተረጉሙት «እንደ መልከ ጻዴቅ ባለ ሹመት የዘለዓለም አገልጋያችን፣ አስታራቂያችን፣ ፊታውራሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደገባበት ውሳጤ መናጦላእት የምታገባ ሃይማኖት ናት» ብለዋል። (እንድምታ ትርጓሜ ዕብራውያንን ይመልከቱ)።

እኛም ዛሬ በዚህ ተስፋ ፀንተን ከዮሐንስ ጋር «በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባህርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለበጉ ይሁን» (ራዕ ፭፥፲፫-፲፬) እያልን እንዘምር።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር …. አሜን።

